# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 2 ቁጥር 67 ታህሳስ 07 ቀን 2013ዓ.ም
በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## < <ኢዜማ የአጭር ጊዜ የፖለቲካ ጥቅም ለማግኘት በሚል በረጅም ጊዜ የሚገኘውን ብሔራዊ ጥቅምን በፍፁም አሳልፎ የሚሰጥ ፓርቲ አይደለም ! > >

**አንዱዓለም ሽፈራው**



# ቆይታ

## ‹‹ኢዜማ የአጭር ጊዜ የፖለቲካ ጥቅም ለማግኘት በሚል በረጅም ጊዜ የሚገኘውን ብሔራዊ ጥቅምን በፍፁም አሳልፎ የሚሰጥ ፓርቲ አይደለም!››

### አንድነት ሽፈራው

አንድነት ሽፈራው የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በጀትና ፋይናንስ ኃላፊ እንዲሁም የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ናቸው፡፡ የዛሬው የዜጎች መድረክ የ ‹‹ቆይታ›› አምድ እንግዳ ናቸው፡፡ ከእሳቸው ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንድታነቡት እንጋብዛለን፡፡ መልካም ንባብ!



*የዜጎች መድረክ እንግዳ ለመሆን ፍቃደኛ ስለሆኑ በአንባቢዎቻችን ስም እናመሰግናለን ፡፡*

እኔም፣ እድሉ ስለተሰጠኝ አመሰግናለሁ፡፡

*የበጀትና ፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ ከተዋቀረ ጊዜ ጀምሮ ምን ምን ሥራዎችን ሲከውን ቆይቷል? ይህ ኮሚቴ በሥሩ ምን ያህል ንዑስ ኮሚቴዎችንስ አደራጅቷል?*

የኢዜማ በጀትና ፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ቋሚ ኮሚቴው የሚመራበት የፋይናንስ መመሪያን በምርጫ ወረዳዎችም ሆነ በጽህፈት ቤት ደረጃ አዘጋጅቷል፡፡ የፋይናንስ መመሪያው ከተዘጋጀ በኋላም የፋይናንስ መመሪያውን ወደ ተግባር ለመቀየር የሚያስችሉ ሰነዶችን በድርጅቱ መዋቅር ውስጥ ሁሉ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማሰራጨት ሥራ ላይ እንዲውሉ አድርገናል፡፡ የፋይናንስ እንቅስቃሴው የባንክ ስርአትን የተከተለና ተጠያቂነትንና ግልፅነትን ያሰፈነ እንዲሆን ስለሚያስፈልግ በምርጫ ወረዳም ሆነ በዋና ፅህፈት ቤት ማከናወን እንዲያስችል የባንክ ሂሳቦችን የመክፈት ሥራ ስንሰራ ቆይተናል፡፡

የንብረት እንቅስቃሴያችን ጤናማ፣ መርህንና ሕግን የተከተለ ለማድረግ አስፈላጊ የሚባሉ ሰነዶችን ስናዘጋጅ ቆይተናል፡፡ የእቅድና የበጀት ዕቅዶችንም አዘጋጅተናል፡፡ በአዲስ አበባ ደረጃ ላሉ ምርጫ ወረዳዎችም አቅማቸውን ሊያጎለብት የሚያስችል ስልጠና ሰጥተናል፡፡ ከፋይናንስ ሥራ ጋር ግንኙነት ያላቸውን በየምርጫ ወረዳ የሚገኙ አባላት ጋር የውይይት መድረክ አዘጋጅተን በምርጫ ወረዳ የፋይናንስ መመሪያ ዝግጅት ላይ እንዲሳተፉ፣ ግብአት እንዲሰጡና ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ የሚያደርጉ ሥራዎችን ሥንሰራ ቆይተናል፡፡ እነዚህን ሁሉ ሥራዎች ለመሥራት የፋይናንስ ኮሚቴው በ6 ዘርፎች እንዲዋቀር አድርገናል፡፡

*የምርጫ ወረዳዎች ቁጥጥር ምን ይመስላል? ስንት ዘርፍስ በሥራቸው አለ?*

የምርጫ ወረዳ ቁጥጥር በሁለት መልክ የተከፈለ ነው፡፡ ይህም የሆነው የፓርቲያችን መዋቅር ሁለት መልክ ያለው ስለሆነ ነው፡፡ እነዚህም የመሪ ዘርፍና የሊቀመንበር ዘርፍ ናቸው፡፡ ከመንግሥት ጋር በተገናኘ ያለውን ሥራ የሚሰራው የመሪ ዘርፍ ሲሆን ከድርጅት ሥራ ጋር በተገናኘ ያለውን ሥራ ደግሞ የሚከውነው በሊቀመንበሩ ሥር ያለው ከፓርቲው የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ጋር የሚገናኘው ዘርፍ ነው፡፡ መንግሥትና ፓርቲ ይለያዩ ሲባል መዋቅሩን ብቻ ሳይሆን በመዋቅሩ ውስጥ ያሉ አሰራሮች ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግን ያካትታል፡፡ ስለዚህም ሁለት ዘርፎች እንዲኖሩን አድርገናል፡፡

*የምርጫ ወረዳዎቻቹ ሀብትና ግብአት በምን መልክ ነው የሚያሰባስቡት? የሚሰባሰበው ሀብትና ግብአት ለታለመለት አላማ መዋሉንስ በምን መልክ ነው የምታረጋግጡት?*

ሀብትና ግብአት የማሰባሰቡን ሥራ የምርጫ ወረዳዎች ራሳቸውን ችለው እንዲከውኑት ለማድረግ ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡ ሥራው በትክክል መሠራቱን ለማረጋገጥ ያዘጋጀነው የፋይናንስ መመሪያም አለ ፡፡ መመሪያውን ወደ ተግባር የመቀየሪያ ቅፆችና ሰነዶች አሉ፡፡ እያንዳንዱ የምርጫ ወረዳ ይህንን ለመተግበር የሚያስችለው ግብአቶች እንዲደርሱት አድርገናል፡፡ ከምርጫ ወረዳዎችና ከዞን አስተባባሪዎች ጋር በነበረን ቆይታ ግብአትና ሀብት ማሰባሰብ ብቻ ሳይሆን ግብአት ከማሰባሰብ በፊት እያንዳንዱ የምርጫ ወረዳ፣ የምርጫ ዘመቻውን እንዲሸከም ማድረግ የሚችልበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ተወያይተናል፡፡ የምርጫ ወረዳዎች የምርጫ ዘመቻን እንዲሸከሙ ለማድረግ የሚያስችሉበት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ ነው፤ ሀብትና ግብአት ማሰባሰብ የሚያስፈልገው፡፡ ምን ያህል የግብአት አይነቶች ያስፈልጋሉ? በምን አይነት ቅደም ተከተል ነው ልናገኛቸው የሚገባው? የሚለውን ለመመለስ የምርጫ ወረዳዎች ቁጭ ብለው አስበው እቅድ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ እቅዳቸውን ካዘጋጁ በኋላም ይህንን ወደ ተግባር ለመቀየር የሚያስችል የሰው ሀይል ማዋቀር ይኖርባቸዋል፡፡ አስፈላጊ የሚባለው የሰው ሀይል ከተዋቀረ በኋላ ከምርጫ ወረዳቸው አንጻር ተስማሚ የሆኑ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶች ምንድናቸው? የሚለውን መለየት መቻል አለባቸው፡፡

ኢዜማ ያስቀመጠው የገቢ ማሰባሰቢያ ሰንሰለት ሥርአት አለ፡፡ ምርጫ ወረዳዎች ያንን ሰንሰለት በመጠቀምም ሀብትና ግብአት ማሰባሰብ ይችላሉ፡፡ ሀብትና ግብአት ለማሰባሰብ የሚያስችሏቸውን ግብአቶችን አሟልተን ማቅረብ ችለናል፡፡ የሚሰባሰበው ሀብትና ግብአት ለታለመለት አላማ መዋሉን የምናረጋግጠውም ያዘጋጀነውን የፋይናንስ አሰራርና መመሪያ መሰረት በማድረግ ነው ፡፡ መመሪያውን በመከተል የሚሰባሰበው ሀብትና ግብአት ለታለመለት አላማ እየዋለ ነው አይደለም የሚለውን የማረጋገጥ ሥራ እንሰራለን፡፡

*ባሳለፍነው የ2012 ዓ.ም ሀብትና ግብአት አሰባሳቢ ኮሚቴ በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል የራት ፕሮግራም በማዘጋጀት አንድ የገቢ ማሰባሰቢያ ማካሄዱ ይታወሳል፡፡ በወቅቱ ከአዲስ አበባ በተጨማሪ በሌሎች የክልል ከተሞችም የገቢ ማሰባሰብ ለማካሄድ እቅድ እንዳለ በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል በተሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ተነግሮ ነበር ፡፡ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞቹ ሊካሄድ ያልቻሉበት ምክንያት ምንድነው?*

ባሳለፍነው ታህሳስ 2012 ዓ.ም ያልከውን ገቢ ማሰባሰቢያ አካሄደን ነበር፡፡ ኢዜማ ከምርጫ ጋር በተገናኘ ያለ ሥራ የሚከውን የምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ አለው፡፡ ይህ ኮሚቴ በወቅቱ የነበረውን የምርጫ ሰሌዳ ከግምት በመከተት ሀብትና ግብአት ማሰባሰቡን የሚመራ ቡድን አዋቅሮ ወደ ተግባር ገብቶ ነበር፡፡ በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል የተካሄደው የገቢ ማሰባሰቢያ የሆነው የራት ፕሮግራም፣ የምርጫ ዘመቻውን ሊመራ የሚያስችል ግብአት በኢዜማ እጅ ላይ ስላልነበረ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ተብሎ የተዘጋጀ የገቢ ማሰባሰቢያ ነው፡፡ ወደ የካቲት 2012 አካባቢ በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች ክልል ከተሞች ሌሎች የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶች ለማካሄድ ቅድመ ዝግጅት ውስጥ ሆነን ሳለ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ሊከሰት ችሏል፡፡ በዚህም ምክንያት የገቢ ማሰባሰቢያውን ማካሄድ ሳንችል ቀርተናል፡፡ ይሄ ማለት ግን ለፓርቲው ሥራ የሚያስፈልጉ ሌሎች ግብአቶችን እያሰባሰብን አልነበረም ማለት አይደለም፡፡ ከኮሮና ጋር በተገናኘ ብዙ ነገሮችን መሥራት ባንችልም የፓርቲውን ዋና ቢሮ የማሳደስና ለቢሮው የሚያስፈልጉ ግብአቶችን የማሰባሰብ ሥራ ስንሰራ ቆይተናል፡፡ ከጽህፈት ቤት እደሳና ሌሎች ሥራዎችን ለመሥራት የሚያስፈልጉንን ወጪዎቻችንን ለመሸፈን ከግለሰቦችም ሆነ በውጪ ከሚገኙ የድጋፍ ቻፕተሮቻችን ድጋፍ እያሰባሰብን ወጪዎቻችንን ስንሸፍን ቆይተናል፡፡

*በያዝነው ዓመት ይካሄዳል ተብሎ የሚጠበቀውን ሀገር አቀፍ ምርጫ ተከትሎ ሀብትና ግብአት አሰባሰብ ኮሚቴ እያደረገው ያለው ዝግጅት ምን ይመስላል?*

ሀብትና ግብአት አሰባሰብ ኮሚቴ አጠቃላይ የምርጫውን እንቅስቃሴ ውጤታማ ለማድረግ በምን መልኩ መሄድ አለበት የሚለውን ለመመለስ የእቅድና የበጀት ዝግጅት ሲያደርግ ነው የቆየው ፡፡ በእቅድና በበጀት ዝግጅቱ መሰረት ምርጫውን የተሳካ ለማድረግ በማዕከል ደረጃ ምን ያህል ግብአት ያስፈልጋል? በክልል ደረጃ ለምናደርገው እንቅስቃሴ ምን ያህል ግብአት ያስፈልጋል? በወረዳ ደረጃስ ምን ያህል ግብአት ያስፈልጋል? የሚለውን በዝርዝር ኮሚቴው አስቀምጧል፡፡

የገቢ ምንጭ ሊሆኑን የሚችሉት እንደ ምርጫ ቦርድ፣ ውጪ ያሉ ዓለም አቀፍ ቻፕተሮቻችን እንዲሁም በሀገር ውስጥ ያሉ ባለሀብቶች ልናገኝ የምንችለውን ገቢ ግምት ከተን እነሱን ማሳኪያ ስልቶች ነድፈን እንቅስቃሴ ውስጥ ገብተናል፡፡ ድጋፍ ሲደረግ የሚደረገው ድጋፍ በምን ▶


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ታህሳስ 07 ቀን 20113 ዓ.ም
አዲስ አበባ

መልኩ ነው ፓርቲው ጋር መድረስ ያለበት የሚለውን መንገድ እያመቻቸን ነው ያለነው :: ከግለሰቦችም ሆነ ከተቋማት ድጋፍ እያገኘንም ነው ያለው፡፡

*አንዳንድ አካላት ኢዜማ ያለውን ሰፊ መዋቅር ከግምት ከተው ማኅበራዊ መሰረት በሌለው ቦታ ላይ ሀብቱን ማባከን የለበትም ይላሉ፡፡ እርስዎ ይህንን አስተያየት እንዴት ይመለከቱታል?*

ይሄ ሀሳብ በተወሰነ ደረጃ እውነት ያለው ይመስላል፡፡ ይህ አስተያየት የኢዜማን ድርጅታዊ መዋቅር ወይም አደረጃጀት በተወሰነ መልኩ ካለመረዳት የመነጨም ይመስላል፡፡ የኢዜማ ዋና የድርጅቱ መሰረትና መዋቅር ምርጫ ወረዳዎች ናቸው፡፡ ምርጫ ወረዳዎቹ የራሳቸው የሰው ሀይል፣ ቁሳቁስም ሆነ ሌሎች ምርጫ ወረዳዎችን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በሙሉ የማሟላት ሙሉ ኃላፊነትና ስልጣን ተሰጥቷቸዋል :: ሀብትም ሆነ ግብአት ለማሰባሰብ የሚንቀሳቀሱት ደግሞ አካባቢያቸው ላይ ያሉ ሪሶርሶችን በመጠቀም ነው፡፡ በዚህም መሰረት እያንዳንዱ የምርጫ ወረዳ የራሱን አካባቢ ሀብትና የሰው ሀይል ስለሆነ የሚጠቀመው ሀብት ይባክናል የሚለው አስተያየት ብዙም ውሀ የሚቋጥር አይደለም፡፡

> ‹‹የኢዜማ ዋና የድርጅቱ መሰረትና መዋቅር ምርጫ ወረዳዎች ናቸው፡፡ ምርጫ ወረዳዎቹ የራሳቸው የሰው ሀይል፣ ቁሳቁስም ሆነ ሌሎች ምርጫ ወረዳዎችን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በሙሉ የማሟላት ሙሉ ኃላፊነትና ስልጣን ተሰጥቷቸዋል :: ሀብትም ሆነ ግብአት ለማሰባሰብ የሚንቀሳቀሱት ደግሞ አካባቢያቸው ላይ ያሉ ሪሶርሶችን በመጠቀም ነው፡፡››

ከላይ ያለውን አስተያየት የሚያቀርቡ አካላት ኢዜማ ምርጫውን እንዴት ነው የሚመለከተው የሚለውንም ማየት ይኖርባቸዋል፡፡ ኢዜማ ምርጫውን እንደ ግብ ነው የሚያየው ወይስ ወደ ግቡ መድረሻ መሳሪያ አድርጎ ነው የሚመለከተው? የሚለውን ማየት ይገባል ፡፡ በእኔ አረዳድ ኢዜማ ይህንን ምርጫ የሚመለከተው ወደሚፈልግበት ግብ መድረሻ አድርጎ ነው፡፡ ከምርጫው ጋር በተገናኘ ልንደርስበት የምንፈልገው ግብ አለ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት መመስረት የሚቻልበትን መሰረት መጣል አንደኛው ግብ ነው፡፡ ሁለተኛው ግብ ደግሞ ሀገራችን ካለችበት የሰላምና የደኅንነት እጦት አውጥቶ የተረጋጋችና ሰላም የሰፈነባት ሀገር ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህም ይህንን ምርጫ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት የመገንባት ሥራ ማስጀመሪያ እንዲሁም የሀገር ሰላምና ደሕንነት መወሰኛ አድርገን ከተመለከትነው ይህንን ማድረግ የሚቻለው ማኅበራዊ መሰረት አለኝ ብለህ በምታስባቸው ቦታዎች ብቻ በመንቀሳቀስ አይደለም፡፡ ማኅበራዊ መሰረት የለኝም ተብለው በሚታሰቡ ቦታዎች ላይ ድርጅታዊ አቅም ለመፍጠር ሀሳብና አመለካከትህን ለማኅበረሰቡ ማድረስ ይገባል፡፡ ማኅበራዊ መሰረት አለኝ ብለህ በምታስባቸው ቦታዎች ብቻ በምታደርገው እንቅስቃሴ ሀገሪቷን ወደ ሰላም አይወስዳትም :: የሀገሪቷ አጠቃላይ ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም የዴሞክራሲያዊ ሥርአት ግንባታ የሚረጋገጠው እያንዳንዱ ዜጎች በሚያደርጉት እንቅስቃሴና ተሳትፎ ነው ከተባለም ኢዜማ በሚችለው ልክ ሙከራ ማድረግ አለበት፡፡

*ምርጫው ወደ ግባችሁ የሚወስዳችሁ መሳሪያ ነው እንጂ ምርጫውን ማሸነፍ ብቻውን ግብ አድርጋችሁ አትመለከቱትም ማለት ነው?*

ምርጫ ማሸነፍ ብቻውን ግብ ሊሆን አይችልም፡፡ ምርጫ አሸንፈን ሀገሪቷን አረጋግተን መምራት የምንችልበት ሁኔታ መፍጠር የማይቻል ከሆነ ምርጫውን ማሸነፍ ብቻ ወደምንፈልገው ግብ አያደርሰንም፡፡ ይህ ማለት ግን ምርጫ ማሸነፍ አያስፈልግም ወይም ምርጫ ላለማሸነፍ ነው የምንሰራው ማለት አይደለም፡፡ በእኔ ዕይታ ምርጫ ወደ ግብ የሚያደርስ መንገድ ነው እንጂ በራሱ ግብ ሊሆን አይችልም፡፡

*የኢዜማ ምርጫ ወረዳዎች ራሳቸውን ችለው የሚንቀሳቀሱ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህ አይነቱ አደረጃጀት በፖለቲካ ፓርቲዎች እምብዛም የተለመደ አይደለም፡፡ ይህ አይነቱ አደረጃጀት አዲስ እንደመሆኑ መጠን ፈተና አልሆነባችሁም? ወረዳዎችስ ይህን አደረጃጀት በሚገባ ተረድተው ያለማዕከሉ ድጋፍ ራሳቸውን ችለው በምን ያህል መንገድ እየተንቀሳቀሱ ይገኛል?*

አደረጃጀቱ አዲስ እንደመሆኑ ፈተና አለው፡፡ እንደሚታወቀው ኢዜማ የተመሰረተውም የተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲዎች ራሳቸውን አክስመው ነው፡፡ የከሰሙት ፓርቲዎች ኢዜማን ቢመሰርቱም የለመዱትን የፖለቲካ ባህል ይዘው ነው የሚመጡት :: በዚህ የተነሳ የተለያዩ ፈተናዎች ያጋጥማል :: ፈተና አጋጠመኝ ብለህ ግን ባለመድከው መንገድ መሄድን አታቆመውም፡፡ ይህ አይነቱ አደረጃጀትም ሆነ መዋቅር ሲዘረጋ ፈተናዎችን የማለፊያ መንገዶችንም አብሮ ነው ያዋቀረው፡፡ አዲስ አደረጃጀት ይዘህ ስትመጣም ፈተናዎች እንደሚያጋጥሙ አውቀህ ነው የምትጀምረው፡፡ ፈተናዎቹ መፈጠራቸውም ተፈጥሯዊ ናቸው፡፡

*የፋይናንስ መመሪያ ላይ ስልጠና መስጠታችሁ ይታወቃል፡፡ ከፋይናንስ መመሪያው ስልጠናስ ምርጫ ወረዳዎች ምን ግብአት አግኝተዋል? የፋይናንስ መመሪያው ምን ያህል ለሥራ ምቹስ ነው?*

የፋይናንስ መመሪያ ብለን ስናዘጋጅ የፓርቲውን የንብረትና የፋይናንስ እንቅስቃሴ ማስተዳደር የሚያስችል የፋይናንስ መመሪያ ነበር ያዘጋጀነው፡፡ ይህ ማለት ግን የፋይናንስም ሆነ የንብረት እንቅስቃሴው በማዕከል ደረጃና በምርጫ ወረዳ ሲሆን አንድ አይነት ነው ማለት አይደለም፡፡ ስለዚህም ከምርጫ ወረዳዎች የፋይናንስ አሰራር ጋር የተቀራረበና ፋይናንሱን ውጤታማ በሆነ መልኩ ማሰራት የሚችል ራሱን የቻለ መመሪያ አዘጋጅተን ነበር፡፡ ያዘጋጀነው መመሪያ ለምርጫ ወረዳዎች እንቅፋት እንዳይሆንም መመሪያው ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ግብአት እንዲሰጡን ጠይቀናቸዋል፡፡ ስልጠናው ስለ ፋይናንስ



መመሪያው ግንዛቤ ማስጨበጫ ብቻ ሳይሆን በመመሪያው ላይ ከምርጫ ወረዳዎች ሀሳብና አስተያየት የተቀበልንበትም ነበር፡፡

ፋይናንስ የሚመራው በሕግና በመርህ ነው፡፡ ሕግና መርሆቹን በአግባቡ ማወቅ ይጠበቃል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲ ስለሆነ ተብሎ የተለየ የፋይናንስ አሰራር አይኖርም :: መሰረታዊ የሚባሉ የፋይናንስ መርሆችን ተከትለው ምርጫ ወረዳዎችም ሥራዎችን መከወን አለባቸው፡፡ ስልጠናውም ይህንን ግንዛቤ እንዲጨብጡ የሚያደርግ ነበር፡፡

የፋይናንስ መመሪያው በተቻለ መጠን አሰሪ እንዲሆን ብለን ከምርጫ ወረዳዎች አስተያየት ተቀብለናል፡፡ መሬት ላይ ያለውን ሀቅም ግንዛቤ ውስጥ የከተተ እንዲሆን አድርገናል፡፡ ወደ ıı የሚጠጉ አንቀፆች ላይ የምርጫ ወረዳዎችን ሀሳቦች ተቀብለን የእነሱን ሀሳብ ማካተት ችለናል፡፡ በቋሚ ኮሚቴ ውስጥ ያሉ አባላትም ተሳትፎ አድርገውበት የተሰራ ነው፡፡ የፋይናንስ መመሪያ ማሻሻያ አዘጋጅተንም ለብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በጽህፈት ቤት በኩል ልከናል፡፡ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ከገመገመው በኋላና ከተሻሻለ በኋላ የበለጠ የሚያሰራ ይሆናል ባይ ነኝ፡፡

*ኢዜማ ተቋማዊ ቅርፅ እንዲኖረው የተሰራው ሥራ እንዴት ይገመግሙታል?*

ኢዜማ ሲመሰረት የእውነት ተቋም እንዲሆን ታስቦበት የተቋቋመ ድርጅት ነው ብዬ ነው የማምነው፡፡ የተለያዩ ፓርቲዎች ራሳቸውን አክስመው የመሰረቱት ፓርቲ ነው፤ ኢዜማ፡፡ ከተመሰረተ በኋላም ሌሎች ፓርቲዎች ራሳቸውን አክስመው ተቀላቅለውታል፡፡ ኢዜማ በተቃውሞ ጎራ ያሉ ፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ በሀገራችን ለሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ ያልተለመደና ያልነበረ አደረጃጀት ይዞ መምጣቱ ለተቋማት ግንባታ የራሱን ሚና ይጫወታል፡፡

የመመሪያ፣ የመዋቅር፣ የቴክኖሎጂና የግብአት ፍላጎቶችን በማሟላት ተቋማዊ ቅርፅ እንዲኖረው ለማድረግ እየተሰራ ነው የሚገኘው፡፡ የፈለገውን ያህል ብትንቀሳቀስ ተቋም መገንባት በአጭር ጊዜ ውስጥ የምታሳካው ተግባር አይደለም፡፡ ከወቅቱና ከጊዜው ጋርም የሚቀያየር የረጅም ጊዜ የሥራ ሂደት ነው፡፡

*ኢዜማ ለሕዝቡ ፖሊሲን መሰረት ያደረገ ፖለቲካ ነው የሚያስፈልገው ብሎ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡ አንዳንድ ወገኖች ይህን የኢዜማ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ከግምት የከተተ አይደለም ሲሉ ይወቅሱታል፡፡ የኢትዮጵያ ፖለቲካ በዘር የታጠረ እንደመሆኑ መጠን በፖሊሲ ክርክር የሕዝቡን ቀልብ መሳብ አይቻልም፡፡ ስለዚህም የፖሊሲ ክርክር በዚህ ወቅት ላይ አካሄዳለው ማለት ዘመኑን ያልዋጀ እንቅስቃሴ ነው ይላሉ፡፡ ለዚህ ትችት ምን ምላሽ አሎት?*

የኢትዮጵያን ፖለቲካ ባህል መቀየር ከኢዜማ አንዱ ፍላጎቶች መሀል ነው፡፡ ኢዜማ የአጭር ጊዜ የፖለቲካ ጥቅም ለማግኘት በሚል በረጅም ጊዜ የሚገኘውን ብሔራዊ ጥቅምን በፍፁም አሳልፎ የሚሰጥ ፓርቲ አይደለም፡፡ መክፈል ያለብንን ዋጋ ሁላ ከፍለን የኢትዮጵያን ፖለቲካ ባህል ለመቀየር እንሰራለን፡፡ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ባህል ሳንቀይር የተረጋጋ ሀገር መፍጠር አይቻለንም፤ ዘላቂነት ያለው ዴሞክራሲያዊ ሥርአት መገንባትም አንችልም፡፡ ለአጭር ጊዜ ፖለቲካ ጥቅም በሚል በረጅም ጊዜ ልናሳካው የምንፈልገውን ነገርና ልንገነባ የምንፈልገውን የፖለቲካ ባህል በፍፁም እንዲነካ ማድረግ የለብንም፡፡

‹‹ሳይለንት ማጆሪቲ›› የሚባለው የማኅበረሰብ ክፍል የሀገሪቷ ፖለቲካ ወዴት እንዲሄድ ይፈልጋል የሚለው ገና አልተፈተነም፡፡ በምርጫው የምናየው ነው የሚመስለኝ፡፡ ሳይለንት ማጆሪቲው የተደራጀ ስላልሆነ በዘር ፖለቲካ አራማጆች እየተደፈቀ ስለሆነ ነው እንደዛ አይነት ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚቻለው ወይስ የማኅበረሰቡ ፍላጎት እንደዛ ስለሆነ ነው? ይህንን ማጥናት ያስፈልጋል።

ባለፉት ሁለት፣ ሶስት ዓመታት በሀገራችን በተፈጠሩ ሁነቶች ማኅበረሰቡ ሁኔታዎችን የተረዳ ይመስለኛል፡፡ እያንዳንዱን ነገር በዘር ቃኝቶ መንቀሳቀስ ኢትዮጵያን ወዴት ሊወስዳት እንደሚችልና ምን አይነት አደጋ ይዞብን ሊመጣ እንደሚችል በግልፅ አይተናል፡፡ ሕወሓት የሚባል የዚህ ታሪክ አስተሳሰብ ባለቤት ምን አይነት ችግር እንደፈጠረና ምን አይነት ችግር ይዞብን እንደመጣ ማኅበረሰቡ በትክክል የተረዳ ይመስለኛል፡፡ ስለዚህ ኢዜማ እየሄደበት ያለው መንገድ ብቸኛ አማራጭ እየሆነ የሚወጣ ይመስለኛል፡፡ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎችም ራሳቸውን በዚህ መልኩ ካላዘጋጁ አስቸጋሪ ነው የሚሆነው፡፡ ፖለቲካ በሀሳብ ፉክክር የምታደርግበት እንጂ በዘር ወይም እምነትን መሰረት ባደረገ አደረጃጀት የምትፎካከርበት መድረክ አይደለም፡፡

*ለነበረን ቆይታ በአንባቢዎቻችን ስም አመሰግናለሁ፡፡*

እኔም አመሰግናለሁ፤በርቱ!

# በመተከል እና በወለጋ በተደጋገሚ ዜጎችን ከሞት መታደግ አለመቻል ለችግሩ የተሰጠው ትኩረት ማነስ ውጤት ነው!

## የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በመተከል እና በወለጋ በጠፋው የሰው ሕይወት የተሰማንን ጥልቅ ሐዘን እንገልጻለን።

በንፁሃን ዜጎች ላይ በተለይ በሁለቱ አካባቢዎች በተደጋጋሚ እየደረሰ ያለው አሰቃቂ ግድያ ማቆሚያ ያልተገኘለት ለጉዳዩ ከተሰጠው የትኩረት ማነስ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል።

በአለፉት ስድስት ወራት በተደጋጋሚ በነዚሁ ቦታዎች ላይ ከስብዕና ውጪ የሆኑ አሰቃቂ ድርጊቶች ንፁሃን ላይ የተፈፀመ ቢሆንም እንዳይደገሙ የተወሰዱ እርምጃዎች ችግሩን የሚመጥን ባለመሆናቸው እና የዜጎችን ደህንነት መጠበቅ ባልቻሉ በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች ላይ ተጠያቂነትን ማስፈን ባለመቻሉ ክቡር የሆነው የሰው ሕይወት በየቀኑ እየጠፋ፣ ቤተሰብ እየፈረሰ እና ማኅበራዊ ሰንሰለታችን እየተበጠሰ፣ በአካባቢው የሚኖሩ ዜጎች የፌደራልም ሆነ የክልል መንግሥታት በሕይወት የመቆየት ዋስትናን ሊሰጡን አይችሉም ብለው እንድያምኑ የሚገደዱበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል።

ድርጊቶቹ መደጋገማቸው፣ የፌደራልም ይሁን የክልል መንግሥታት እና የፀጥታ አካላት ንፁሃን ላይ የሚደርሱ አደጋዎች ከመድረሳቸው በፊት አስቀድሞ የመከላከል፣ አደጋዎቹ ሲከሰቱ ከባድ ጉዳት ሳያደርሱ የመቆጣጠር እንዲሁም ከደረሱ በኋላ አስተማሪ የሆነ እርምጃ የመውሰድ አቅማቸው ከፍተኛ ክፍተት እንዳለበት በግልፅ የሚያሳይ ነው።

ኢዜማ ከዚህ ቀደም መስከረም 7 እና ጥቅምት 16 ቀን 2013 ዓ.ም በእነዚህ አካባቢዎች ንፁሃን ላይ የደረሱ ጥቃቶችን ተከትሎ በሰጠው መግለጫ ግልፅ እንዳደረገው፣ ዜጎች መሰረታዊ የሆነው በሕይወት የመቆየት መብታቸው ካልተከበረ ሕይወታቸውን ለማሻሻል እና የነፃነት አድማሳቸውን ለማስፋት በብዙ ልፋት የሚሠሩ ሌሎች ተግባራት ፍፁም ትርጉም አይኖራቸውም። በመሆኑም እስካሁን ለደረሱት ጥቃቶች ተጠያቂነትን ማስፈን እንዳለ ሆኖ የዜጎችን ደህንነት የመጠበቅ ተቀዳሚ ኃላፊነት ያለባቸው የአካባቢ አስተዳደሮች እንዲሁም በየደረጃው የሚገኙ የመንግሥት መዋቅሮች እና የፀጥታ አካላት እርስ በርስ ጣት መጠቋቆም አቁመው ከአሁን በኋላ በምንም ምክንያት ተመሳሳይ ድርጊቶች እንዳይደገሙ ማድረግ የሚገባቸውን ሁሉ እንዲያደርጉ እና የንፁሃን ዜጎችን ሕይወት ከአደጋ በመከላከል ከሕግም ከህሊናም ተጠያቂነት እራሳቸውን እንዲያድኑ እናሳስባለን። ይህ ሳይሆን ቢቀር ግን በተደጋጋሚ ጥቃት የደረሰባቸው ዜጎች በመንግሥት ጨርሶ ተስፋ እንዲቆርጡ እና ደህንነታቸውን የመጠበቅ ኃላፊነት በራሳቸው እንዲወጡ በመግፋት ወደማንወጣው እና ታሪካዊ ጠባሳ ወደሚጥል አዘቅት ውስጥ ሊከተን የሚችል ከፍተኛ አደጋ እንደተጋረጠብን ልናውቅ ይገባል።

የኢዜማ አባላት እና አመራሮች በሞቱት ወገኖቻችን የተሰማንን ሐዘን እየገለፅን ለወዳጅ ዘመዶቻቸው እና ለመላው ኢትዮጵያውያን ልባዊ መፅናናትን እንመኛለን። በዚህ አጋጣሚ በአካባቢዎቹ የሚከሰቱ ጥቃቶችን ማስቆም የሚቻልበት መፍትሄ ለመፈለግ በመዋቅሩ በኩል ከአካባቢው ነዋሪዎች የጀመረውን ምክክር እንደሚቀጥል እና የደረሰበትን ውጤት ለሚመለከታቸው አካላት እና ለሕዝብ ይፋ እንደምናደርግ ለማሳወቅ እንወዳለን።

**የኢዜማ ህዝብ ግንኙነት**





# ‹‹ማኅበረሰባዊ ለውጥ ለማምጣትና ወደ ውድቀት ላለመሄድ የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ማረጋገጥ ግድ ይላል››

## ከውሰር አድሪስ

ታኅሣሥ 7 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)




የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን የመከላከል የ16 ቀናት ንቅናቄ ማጠቃለያን አስመልክቶ በአዲስ አበባ ከተማ ‹‹ለሴቶች ምቹ ሀገር›› በሚል መሪ ቃል በተለያዩ የምርጫ ወረዳዎች ሲያካሄድ የነበረውን ውይይት እሁድ ታህሳስ 4 ቀን 2013 ዓ.ም በዋና ጽህፈት ቤቱ በመስፍን ወልደማሪያም አዳራሽ ባካሄደው የፓናል ውይይት አጠናቀቀ፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የተካሄደውን የ16ቱ ቀናት የሴቶችን ጥቃት መከላከል እንቅስቃሴን በተለያዩ ሁነቶች ሲያካሄዱ መቆየቱን የገለፁት የኢዜማ ሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ገነት አራጌ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የዚህ ባለድርሻ ናቸው ብለው ስለሚያስቡ ከተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋርም በጉዳዩ ላይ መወያየታቸውን ጠቁመዋል፡፡ ‹‹ችግሩ የሚቀረፈው የፓናል ውይይቶችን ብቻ በማካሄድ አይደለም›› ያሉት ተጠሪዋ፣ ችግሩ የሚቀረፈው በፖሊሲ ነው ብለው እንደሚያምኑ አስረድተዋል፡፡ ለዚህም ሲባል የሴቶችን ጉዳይ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን ፓርቲያቸው እየቀረፀ እንዳለ አስታውቀዋል፡፡

ማኅበረሰባዊ ለውጥ ለማምጣትና ወደ ውድቀት ላለመሄድ የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ማረጋገጥ ግድ እንደሚል የሚናገሩት የኢዜማ የምርጫና ስትራቴጂ ኮሚቴ ፀሐፊ የሆኑት ከውሰር እድሪስ፣ ‹‹ማኅበረሰብ መቀየር ከፈለገ ሴቶችን መቀየር አለበት›› ብለዋል፡፡ ፀሐፊዋ፣ እንደ ማኅበረሰብ ለመቀጠል ከተፈለገም ሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎ ማድረግ ይገባቸዋል በማለት ከመገናኛ ብዙሀን ለተነሳላቸው ጥያቄ ምላሻቸውን ሰንዝረዋል፡፡

በያዝነው ዓመት ይካሄዳል ተብሎ በሚጠበቀው ሀገር አቀፍ ምርጫ ላይም ተሳታፊ የሚሆኑ ሴቶችን የመመልመልና ሴቶች ለምርጫው ብቁ ሆነው እንዲወጡ የማድረግ ሥራ እንደሚሰሩ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪዋ ገነት አራጌ ለዜጎች መድረክ ተናግረዋል፡፡

# ‹‹ሴቶች ለምርጫው ብቁ ሆነው እንዲወጡ የማድረግ ሥራ ይሰራል››

## ገነት አራጌ (የኢዜማ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ)

ታኅሣሥ 7 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



ፎቶ፡- ከፋይል

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማክሰኞ ታህሳስ 06 ቀን 2013 ዓ.ም በረቂቅ የፖለቲካ የሥርዓት-ፆታ ኦዲት ሠነድ በማስመልከት ባዘጋጀው የምክክር መድረክ ላይ በመሳተፍ ሴቶች በቀጣዩ ምርጫ ሰፊ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችል ሥራ መሥራት እንደሚገባ ሃሳብ መስጠቱን የኢዜማ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ገነት አራጌ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በረቂቅ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሥርአተ-ፆታ ኦዲት ሰነድ ላይ ግብአት ለመሰብሰብ የሚያስችለውን መድረክ፣ የቦርዱ አመራሮች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪክ ማኅበራት ተወካዮች በተገኙበት ነው ያካሄደው፡፡ በእለቱ የቦርዱ ዋና ሰብሳቢ የሆኑት ብርቱካን ሚደቅሳ ውይይቱን ንግግር በማድረግ ከፍተዋል፡፡ በንግግራቸውም «ኦዲቱ ያለንበትን የምናውቅበት ብቻ ሳይሆን ለምን እዛ ሆንን ብለን የምንጠይቅበት ነው» ብለዋል፡፡

የሠነድ ሪፖርቱ ከቀረበ በኋላ በቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ በውብሸት አየለ እና እመዛት መንገሻ መሪነት ውይይት ተካሄዷል፡፡ ከመድረኩ ተሳታፊዎችም የተለያዩ አስተያየቶችና ጥያቄዎችም ተነስተው፤ ተስተናግደዋል፡፡

በውይይቱ ላይ ሴቶች ወደ ፖለቲካ ተሳትፎ እንዲመጡ በቅድሚያ የፖለቲካ መረጋጋት መፍጠር እንደሚገባ የገለፁት የኢዜማ ሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ገነት አራጌ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለምርጫ የሚወዳደሩ እጩዎች ሁለት ወራት ከሥራ ገበታቸው ውጪ ሆነው መሳተፍ እንዳለባቸው ያስቀመጠው መመሪያ በድጋሚ ማየትና መከለስ እንደሚገባው ጠቁመዋል፡፡

ቦርዱ የሴቶችን ተሳትፎ 30 በመቶ ለማሳደግ በሚሰራው ሥራ ኢዜማ የበኩሉን ድርሻ እንደሚወጣ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪዋ አስታውቀዋል፡፡





# ኢዜማ በዴሞክራሲ ተቋማት ላይ የሚያደርገውን ግምገማ ጀመረ

ታኅሣሥ 7 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



ፎቶ፡- ከፋይል

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በዴሞክራሲ ተቋማት ላይ የሚያደርገውን ግምገማ መጀመሩንና ሥራውንም በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ እንዳቀደ የኮሚቴው አባል የሆኑት ባንቲገኝ ታምራት (ዶ/ር) ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

የዴሞክራሲ ተቋማት ግምገማ ለማካሄድ ቀደም ተብሎ ዝግጅት ተጀምሮ እንደነበር ያወሱት ባንቲገኝ ታምራት፣ በሀገሪቱ ያለው ነባራዊ ሁኔታ እንዲሁም የኮሚቴው ሰብሳቢ ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ በሆነው የኮሮና ቫይረስ ምክንያት በሙያቸው ለሀገራቸው ሰፊ አገልግሎት እየሰጡ በመቆየት ላይ ስለነበሩ፣ የኮሚቴው አባላት ተገናኝተው መሥራት አለመቻላቸውን አስረድተው፤ አሁን ላይ ግን ባሉት የኮሚቴው አባላት ሥራ መጀመራቸውን ጠቁመዋል፡፡

በዚህ ሥራ ላይ በእያንዳንዱ ዘርፍ በሙያቸው ድጋፍ የሚያደርጉ ሰዎች ተሳትፈው እየሰሩ እንደሚገኙ የጠቀሱት የኮሚቴው አባል፣ ፖሊስ፣ ፍርድ ቤቶች፣ ምርጫ ቦርድ፣ ሰብዓዊ መብት ተቋማትና ሚዲያዎች ላይ ግምገማ እንደሚያካሄዱ ተናግረዋል፡፡

ኮሚቴው ሥራውን ጨርሶ ለሕዝብ መች ይፋ ሊያደርግ ይችላል? በሚል ከዜጎች መድረክ ለተነሳው ጥያቄ የኮሚቴው አባል በሰጡት ምላሽ ሥራቸውን ሰርተው ሲጨርሱ ለብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሪፖርት እንደሚያቀርቡ ጠቁመው፣ ለሕዝብ ይፋ መሆን ካለበትም በብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ በኩል ይፋ እንደሚሆን ተናግረዋል፡፡

---

# ኢዜማ የምርጫ አስፈጻሚ አባላት ምልመላን በተመለተ ምርጫ ቦርድን ማብራሪያ ጠየቀ

ታኅሣሥ 8 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ምርጫ ቦርድ በግልጽ ባላስቀመጠው ሁኔታ የአማራ ክልልና የደቡብ ክልል፣ የምርጫ አፈጻጸም ላይ የሚሳተፉ ሰዎችን ማስታወቂያ በማውጣት እየቀጠሩ እንደሚገኙ ስለደረሰበት በጉዳዩ ላይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማብራሪያ እንዲሰጠው ጠየቀ፡፡

የምርጫ አስፈጻሚ አባላትን የመመልመል፣ የማሰልጠንና የማሰማራት ሥልጣን በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7.15 በሚዘረዝረው አንቀጽ መሠረት ሥልጣንና ተግባሩ የምርጫ ቦርዱ መሆኑን የገለፁት የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ፣ በማይመለከታቸው አካላት ቅጥር ለመፈፀም ሙከራ መደረጉ አግባብ አለመሆኑን አስረድተዋል፡፡ በዚህም ሳቢያ ቦርዱ ማብራሪያ እንዲሰጣቸው በደብዳቤ ጥያቄ ማቅረባቸውን ለዜጎች መድረክ ገልፀዋል፡፡

ምርጫ ቦርድ የሚመለምላቸውን የምርጫ አስፈጻሚዎች ለፖለቲካ ፓርቲዎች መግለጽ እንዳለበት የሚደነግግ አንቀጽ ያለ መሆኑን የጠቀሱት ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው፣ በሁለቱ ክልሎች የሚገኙ የወረዳውና የዞኑ ኃላፊዎች መስፈርት በማውጣት የመንግሥትን ማኅተም ጭምር ተጠቅመው ቅጥር መፈጸም መጀመራቸውን አስረድተዋል፡፡ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊው በያዝነው ዓመት ይካሄዳል ተብሎ የሚጠበቀው ሀገር አቀፉ ምርጫ ዴሞክራሲያው ከመሆን ውጪ ሌላ እድል የለውም ያሉ ሲሆን፣ ምርጫው እንደ በፊቱ ተጭበርብሯል ብቻ ተብሎ ሊታለፍ እንደማይችል ገልፀው፤ ሕጋዊ አካል ብቻ በሚያወጣቸው የምርጫ አፈጻጸም መመሪያዎች መጓዝ እንደሚገባ አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል፡፡

ለቦርዱ ገቢ በተደረገው ደብዳቤ ላይ ኢዜማ «ቅጥሩ እየተካሄደ ያለው በምርጫ ቦርድ እውቅና ነው ወይ?» የሚል ጥያቄ በማንሳት ማብራሪያ መጠየቁን የገለፁት የድርጅት ጉዳይ ኃላፊው፣ ድርጊቱ በቦርዱ እውቅና ከሌለው ቦርዱ ቅጥሩን እንዲያስቆም አሳስበዋል፡፡

# < <ኢዜማ በዚህ ደረጃ ቢሮውን ማደሱ ለሌሎች ተከራዮችና ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አስተማሪ ነው።> >

## የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን

ታኅሣሥ 7ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን በኪራይ የተቀበለውን ቢሮ በዘመናዊ መልክ አድሶ መጨረሱን ተከትሎ በአዲስ አበባ ለሚገኙ የኢዜማ የምርጫ ወረዳ አባላትና አመራሮች ቢሮውን ማስጎብኘት መጀመሩን የኢዜማ ዋና ጸሐፊ አበበ አካሉ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

ራሳቸውን አክስመው ኢዜማን የመሠረቱት ፓርቲዎች በፊት ሲጠቀሙባቸውን የነበሩትን ቢሮዎችን ሙሉ ለሙሉ በማስረከብ አሁን ያለውን ቢሮ ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን በኪራይ መቀበላቸውን ያስታወሱት ዋና ፀሐፊው፣ ቢሮውን ሲረከቡ ውስጡ በጣም ተበላሽቶ ስለነበር የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን አንዳንድ ፍሳሽ ነክ ነገሮችን ከማስተካከል ውጭ ሌሎች የእድሳት ሥራዎችን እንደማይሰራ በማሳወቁ ቢሮውን ሙሉ ለሙሉ እንዳደሱት አስረድተዋል፡፡ በአዲስ አበባ የሚገኙ የኢዜማ ወረዳዎች፣ ከሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ የሚገኙ የኢዜማ ደጋፊዎች እንዲሁም የኢዜማን አላማ በሚደግፉ አካላት እገዛ ቢሮውን ማደስ ተችሏል።

ኢዜማ ቢሮውን አጠናቆ ለሥራ ዝግጁ ለማድረግ ከ7 ወራት በላይ የፈጀ ሥራ ሲሰራ ከ5 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ማድረጉን ፀሐፊው ገልፀዋል፡፡

የቢሮው ዋና ዋና ሥራዎች በመጠናቀቃቸው በፓርቲው መሪ ብርሀኑ ነጋና (ፕሮፌሰር) ሊቀመንበሩ የሺዋስ አሰፋ ቢሮውን የማስጎብኘት ሥራ ተጀምሯል። በቀጣይም የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ኃላፊዎችን፣ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችንና ድጋፍ ያደረጉ ደጋፊዎችን የማስጎብኘት ሥራ የሚካሄድ ይሆናል።

የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን፣ ኢዜማ በዚህ ደረጃ ቢሮውን ማደሱን ለሌሎች ተከራዮችና ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አስተማሪ ነው ብሏል።

በቀጣይም የኢዜማ ብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ከቢሮ እድሳት ኮሚቴና ከሕዝብ ግንኙነት ኮሚቴ ጋር በመሆን ቢሮውን የማስመረቂያ ዝግጅት እንደሚያዘጋጅ ለመረዳት ተችሏል።